የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

ለክብርት ዶ/ር ኤርጎጌ ተስፋዬ
የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር
አዲስ አበባ፤

ጉዳዩ:- የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር (የቀድሞ)
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርትን ይመለከታል፣

ከላይ በርዕሱ የተጠቀሰውን ኦዲት ውጤትና አስተያየት የያዘ 3 ገጽ የኦዲት ሪፖርት እና 2 ገጽ የሂሣብ መግለጫዎች በድምሩ 5 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ግርማ በላቸው ታደሰ
የአቅም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት
ዳይሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር (የቀድሞ)

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ሚያዚያ 2015

አዲስ አበባ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር (የቀድሞ)
የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ሪፖርት

ሚኒስቴር መ/ቤቱ የተመደበለትን በጀት ለታቀደለት ዓላማ ማዋሉን፤ እንዲሁም ሂሳቡ በመንግስት የሂሳብ አያያዝ ስርዓት መሰረት መያዙንና የመንግስት ሀብትና ንብረት በሚገባ መጠበቁን ለማረጋገጥ የ2014 በጀት ዓመት (ከሐምሌ 1/2013 - ጥቅምት 30/2014) ሂሳብ ሪፖርቶችን እና የሂሳብ ማስታወሻዎችን ኦዲት አድርገናል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶችን የማዘጋጀት ኃላፊነት **የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር (የቀድሞ)** ሥራ አመራር ሲሆን የሂሳብ ሪፖርቶችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ አስተያየት መስጠት ደግሞ **የፌደራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት** ኃላፊነት ነው፡፡

ኦዲቱ የተከናወነው የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 እና በማሻሻያ ቁጥር 1146/2011 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን ሲሆን፤ ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፦

- የሂሳብ ሪፖርቶች ላይ የሰፈሩትን አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ ሪፖርቶችን ሲያዘጋጅ ያደረገውን ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎችን መመዘንን፣
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ ሪፖርቶች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦች እና በተከታታይ የወጡ መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆኑን በናሙና ኦዲት ማከናወንን ይይዛል፡፡

የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ ከሆኑ ስህተቶች የፀዱ ለመሆኑ በቂ ማስረጃና አጥጋቢ ማረጋገጫ የሚሰጥ መረጃና ማብራሪያ ሊያስገኝ በሚችል መልኩ ኦዲቱን አቅደን አከናውነናል::

ለኦዲቱ ሥራ መሠረት የሆኑት መ/ቤቱ ያቀረባቸው የሂሳብ ሪፖርቶች፣ መዛግብት፣ ደጋፊ ማስረጃዎች እንዲሁም በመ/ቤቱ ሥራ አመራር የተሰጡ ማብራሪያዎች ናቸው::

ኦዲቱ የተከናወነው የበጀት ዓመቱን የሂሳብ እንቅስቃሴ ሊወክሉ የሚችሉ ናሙናዎችን በመውሰድ በጥልቀትና በዝርዝር ኦዲት በማድረግ ነው::

የሚከተሉት የኦዲት ተደራጊው መ/ቤት የሂሳብ ሪፖርቶች ከዚህ የኦዲት ሪፖርት ጋር ተያይዘው ቀርበዋል።

- የገቢ /የዕርዳታ/ የብድር ሂሳብ ሪፖርት፣
- የወጪ ሂሳብ ሪፖርት፣
- የዝውውር ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተሰብሳቢ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የተከፋይ ሂሳቦች ሪፖርት፣
- የሂሳብ ሚዛን ሙከራ፣

<u>ለኦዲት አስተያየቱ መሰረት የሆኑት ጉዳዮች፣</u>

የሴቶች፣ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር (የቀድሞ) የሂሳብ ሪፖርቶች ጉልህ የሆነ ግድፈት የሌለባቸው፣ በአዋጅ በተፈቀደው በጀት እና በመንግሥት ሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት የተዘጋጁ እና የተሰበሰበው ገቢ፣ የተከፈለው ወጪና የበጀት አጠቃቀሙ የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅን፣ ደንብና መመሪያን የጠበቀ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

1. በቀን 23/11/2013 በተጻፈ ደብዳቤ የተወሰኑ ስልኮች ማን እንደሚጠቀምባቸው ባለመታወቁ እንዲዘጉ የተጠየቀ ቢሆንም ማን እንደሚጠቀምባቸው ለማይታወቁ ስልኮች ብር 28,724.47 የስልክ አገልግሎት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፣ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል።

ከላይ ከተገለጸው ሁኔታ በስተቀር የመ/ቤቱ የሂሳብ ሪፖርቶች ጥቅምት 30 ቀን 2014 ዓ.ም የተመለከተውን የፋይናንስ አቋም እና የበጀት ዓመቱን የሥራ እንቅስቃሴ በኢትዮጵያ መንግሥት የፋይናንስ አስተዳደር አዋጅ እንዲሁም የሂሳብ አያያዝ ሥርዓት መሠረት ትክክለኛውን ገጽታ ያሳያሉ።

ምንም እንኳ ከላይ የተሰጠውን የኦዲት አስተያየት የማይቀይረው ቢሆንም ቀጥሎ የተመለከቱት ጉዳዮች ትኩረት ሊሰጣቸው፣ እርምጃ ሊወሰድባቸው እና ለወደፊቱም ጥንቃቄ ሊደረግባቸው ይገባል፡፡

1. ሌሎች ጉዳዮች (Other Matters)፤

1.1. የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት በየበጀት ዓመቱ የመ/ቤቱን ሂሳብ ኦዲት አድርጎ ሙያዊ አስተያየትና የማሻሻያ ሃሳቦች ያቀረበ ሲሆን፣ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት መ/ቤቱ ተገቢውን እርምጃ የወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡- የ2013 በጀት ዓመት ግኝቶች፤

- ብር 200,000.00 የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብለት አላግባብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
- ብር 305,500.00 አላግባብ በድጋሚ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
- ብር 1,188.00 ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብለት የስልጠና ወጪ በሚል አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት

ሚያዚያ 2015

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት
THE FEDERAL DEMOCRATIC
REPUBLIC OF ETHIOPIA
OFFICE OF THE FEDERAL
AUDITOR GENERAL

Ofa97o4.11/21/24.
ቀን 05/08/2015

ለሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር

<u>አዲስ አበባ፤</u>

ጉዳዩ፡- <u>የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር (የቀድሞ) የ2014 በጀት ዓመት የመጨረሻ ሥራ አመራር ሪፖርትን ይመለከታል፤</u>

በርዕሱ የተጠቀሰውን የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር (የቀድሞ) የ2014 በጀት ዓመት ሂሣብ የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦችን የያዘ 4 ገጽ የመጨረሻ የሥራ አመራር ሪፖርት (Final Management Letter) እና 2 ገጽ አባሪ በድምሩ 6 ገጽ ከዚህ ደብዳቤ ጋር አያይዘን የላክን መሆኑን እንገልጻለን፡፡ በመሆኑም በገጽ 7 በተመለከተው የኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሀሳቦች አተገባበር መርሃ-ግብር ቅጽ መሰረት የተወሰዱ እርምጃዎች በአስቸኳይ እንዲላክልን እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ርማ በላቸው ታደሰ
ም ግንባታ መ/ቤቶች ኦዲት
ሬክቶሬት ዳይሬክተር

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር (የቀድሞ)

የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች

መግቢያ፤

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤትን ለማቋቋም በወጣው አዋጅ ቁጥር 982/2008 እና በማሻሻያ ቁጥር 1146/2011 ለመ/ቤታችን በተሰጠው ሥልጣን መሠረት **የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር** የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ላይ የኦዲት አስተያየታችንን ለመስጠት ያስችለን ዘንድ የመ/ቤቱን ሂሳብ ኦዲት አድርገናል፡፡

ዓላማ፤

የዚህ ሪፖርት ዓላማ በኦዲታችን ወቅት የተገኙትን የውስጥ ቁጥጥር ድክመቶች እና ሌሎች ግድፈቶች የመ/ቤቱ የበላይ አመራር አካላት እንዲያውቁትና ተገቢውን የማስተካከያ እርምጃ በመውሰድ ምላሽ እንዲሰጡበት ለማስቻል ነው፡፡

የኦዲቱ ወሰንና ኃላፊነት፤

ኦዲቱ የተከናወነው ዓለም አቀፍ የኦዲት ደረጃዎችን (ISSAI) መሠረት በማድረግ ነው፡፡ እነዚህን የኦዲት ደረጃዎች መከተል ኦዲቱን በሚገባ አቅደን በመሥራት በተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ላይ አጥጋቢ የሆነ የኦዲት አስተያየት ለመስጠት ያስችለናል፡፡

ኦዲታችን፡-

- በሂሳብ መግለጫዎች ላይ የሰፈሩት አሀዞችና መግለጫዎችን የሚደግፉ ማስረጃዎችን በናሙና ኦዲት ማከናወንን፣
- የሥራ አመራሩ የሂሳብ መግለጫዎችን ሲያዘጋጅ ያደረጋቸው ጉልህ ግምቶች እና ውሳኔዎች መመዘንን ፤
- የሂሳብ አያያዝ ፖሊሲዎች ከዓመት ዓመት ሳይቀያየሩ በሥራ ላይ መዋላቸውን እና በበቂ ሁኔታ መገለጻቸውን ማመዛዘንን ያጠቃልላል፡፡

ከዚህም በተጨማሪ የተዘጋጁት የሂሳብ መግለጫዎች ተገቢ የሆኑ አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎችን በመከተል የተዘጋጁ መሆናቸውን ኦዲት ማድረግን ይጨምራል፡፡

ቀጥለው በተመለከቱት የኦዲት ግኝቶች ላይ የማሻሻያ ሃሳቦችን ለመስጠት በሂሳብ መግለጫዎች ላይ ያለውን የመረጃ አቀራረብ አጠቃላይ ብቃት ገምግመናል፡፡ ይሁን እንጂ ኦዲቱ በሴቶች፤

ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የሚታዩትን የውስጥ ቁጥጥርና ሌሎች ድክመቶችን ሙሉ በሙሉ ሊያሳይ አይችልም።

የሂሳብ መግለጫዎችን የማዘጋጀት ኃላፊነት የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር ሥራ አመራር ሲሆን፣ የሂሳብ መግለጫዎችን ኦዲት በማድረግ ሙያዊ የኦዲት አስተያየት መስጠት ደግሞ የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት ኃላፊነት ነው።

የሴቶች፤ ሕፃናትና ወጣቶች ሚኒስቴር የ2014 በጀት ዓመት ሂሳብ ኦዲት ግኝቶችና የማሻሻያ ሃሳቦች ከዚህ በታች እንደሚከተለው ቀርበዋል።

1. <u>የወጪ ሂሳብ</u>፣

በወጪ የተመዘገቡት ሂሳቦች መ/ቤቱ ለተጠቀመበት አገልግሎት መዋሉን፤ የዕቃና አገልግሎት ግዥ በመንግስት የግዥ መመሪያ መሠረት መፈጸሙን፣ የተገዙት ዕቃዎች ገቢ መደረጋቸውን፣ እንዲሁም ለታቀደለት ዓላማ መዋላቸውን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ ቀጥሎ የተመለከቱት ሁኔታዎች ተገኝተዋል።

1.1. <u>የመ/ቤቱ መሆናቸው ላልተረጋገጠ ስልኮች የተፈጸመ የስልክ አገልግሎት ክፍያ ብር 28,724.47</u>፣

1.1.1. <u>ግኝት</u>፣

የፌደራል መንግስት መ/ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 በክፍል ሁለት አንቀጽ 8 ንዑስ አንቀጽ 2ለ የክፍያ ሂሳብ ከመወራረዱ በፊት ስለወጪው የተሟላ ማስረጃ ማቅረብና ስልጣን ባለው አካል መፈቀድ እንዳለበት ይገልጻል። የመ/ቤቱ ሂሳብ ኦዲት ሲደረግ፤

- በቀን 23/11/2013 በተጻፈ ደብዳቤ የተወሰኑ ስልኮች ማን እንደሚጠቀምባቸው ባለመታወቁ እንዲዘጉ የተጠየቀ ቢሆንም ማን እንደሚጠቀምባቸው ለማይታወቁ ስልኮች ብር 28,724.47 የስልክ አገልግሎት ክፍያ የተፈጸመ መሆኑ፤ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል። ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 1 ቀርቧል።

1.1.2. <u>ስጋት</u>፣

የመ/ቤቱ መሆናቸው ላልተረጋገጠ ስልኮች የአገልግሎት ክፍያ መፈጸም ውስን የሆነው የመንግስት ሃብት እንዲባክን ያደርጋል። እንዲሁም ተጠያቂነትን ያስከትላል።

1.1.3. <u>የማሻሻያ ሃሳብ</u>፣

አላግባብ የተፈጸመው ክፍያ ተጣርቶ ከሚመለከታቸው ተመላሽ ሊደረግ ይገባል፡፡ ለወደፊቱም ለክፍያዎች ተገቢ ማስረጃ መቅረቡ እየተረጋገጠ ክፍያ እንዲፈጸም በየጊዜው ተገቢ ቁጥጥር ማድረግ ይገባል፡፡

1.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ</u>፣

በአባሪነት ከተያያዙት የስልክ ቁጥሮች 16 ስልኮች ለኢትዮ ቴሌኮም በተጻፈ ደብዳቤ እንዲዘጉ ተደርጓል፡፡ ይህንንም የሚያስረዳ ማስረጃ ተያይዟል፡፡

1.1.5. <u>የኦዲተር አስተያየት</u>፣

ስልኮቹ እንዲዘጉ ለኢቲዮ ቴሌኮም ከተጻፈ በኂላ በሐምሌ/2013 እና ጳጉሜ/2013 ክፍያ የተፈጸመ በመሆኑ ሁኔታው ተጣርቶ ተገቢ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ማድረግ ይገባል፡፡

2. <u>የክትትል ኦዲት (Follw-up Audit)</u>፤

2.1. <u>እርምጃ ያልተወሰደባቸው ያለፉት በጀት ዓመታት ኦዲት ግኝቶች</u>፤

2.1.1. <u>ግኝት</u>፤

ባለፉት በጀት ዓመታት የኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ የተወሰደ መሆኑን ለማረጋገጥ ኦዲት ሲደረግ፡-

በጀት ዓመት	እርምጃ ሊወሰድበት የሚገባ			እርምጃ የተወሰደበት			እርምጃ ያልተወሰደበት		
	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በፐርሰንት (በ%)	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በፐርሰንት (በ%)	በገንዘብ መጠን	በቁጥር	በፐርሰንት (በ%)
2013	506,688.00		100%	--	--	--	506,688.00		100%
2013		3	100%	--	--	--		3	100%

በኦዲት አስተያየቱ መሰረት በቁጥር ደረጃ ከተገለጹት የአሰራር ክፍተቶች ውስጥ 100% ላይ የማስተካከያ እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡ በገንዘብ ደረጃም እርምጃ ሊወሰድበት ከሚገባው አጠቃላይ የገንዘብ መጠን ውስጥ 100% ላይ የእርምት እርምጃ ያልተወሰደ መሆኑ ታውቋል፡፡ እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች ዝርዝር ቀጥሎ ቀርቧል፡፡

<u>የ2013 በጀት ዓመት ግኝቶች፤</u>

- ብር 200,000.00 የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብለት አላግባብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
- ብር 305,500.00 አላግባብ በድጋሚ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤
- ብር 1,188.00 ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብለት የስልጠና ወጪ በሚል አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤_በኦዲቱ ወቅት ታውቋል፡፡

ከላይ የተዘረዘሩት ግኝቶች ላይ የማስተካከያ እርምጃ እንዲወሰድ ያሳሰብን ቢሆንም የማስተካከያ እርምጃ አልተወሰደም፡፡ **ዝርዝሩ በአባሪ ቁጥር 2 ቀርቧል፡፡**

2.1.2. <u>ሥጋት፤</u>

በተሰጠ የኦዲት አስተያየት መሠረት የማስተካከያ እርምጃ አለመውሰድ በኦዲት ወቅት የታዩ የአሰራር ግድፈቶች እንዳይታረሙ ከማድረጉም ባሻገር ተጠያቂነትን ያስከትላል፡፡

2.1.3. <u>የማሻሻያ ሀሳብ፤</u>

በኦዲት ግኝቶች ላይ በተሰጡት የማሻሻያ ሀሳቦች መሰረት አስፈላጊው እርምጃ እንዲወሰድ በድጋሚ እናሳስባለን፡፡

2.1.4. <u>የሥራ አመራሩ ምላሽ፤</u>

በተሰጠው አስተያየት መሠረት የእርምት እርምጃ የምንወስድ መሆኑን እንገልጻለን፡፡

በመጨረሻም ለተደረገልን መልካም የስራ ትብብር እናመሰግናለን!

የፌዴራል ዋና ... የሰነድና ማህደር ... መ/ቤት

አባሪ 1፡ <u>የመ/ቤቱ መሆናቸው ላልተረጋገጠ ስልኮች የተፈጸመ የአገልግሎት ክፍያ፤</u>

ተ.ቁ	ቀን	የደረሰኝ ቁጥር	ስልክ ቁጥር	የገንዘብ መጠን
1	04/12/2013	13194	011-55-26-021	16.52
2			09-93-82-51-10	1,313.04
3			09-11-21-07-69	10.44
4			09-44-17-64-03	1,565.22
5			09-43-07-19-12	1,313.04
6			09-43-07-19-28	1,313.04
7			09-65-18-10-68	1,313.04
8			09-44-30-30-74	391.30
9			09-44-30-30-75	12.18
10			09-44-36-81-59	1,313.04
11			09-01-02-97-15	1,522.68
12	03/13/2013	13458	011-55-26-021	33.05
13			09-93-82-51-10	2,626.08
14			09-11-21-07-69	17.40
15			09-44-17-64-03	3,130.44
16			09-43-07-19-12	2,626.08
17			09-43-07-19-28	2,626.08
18			09-65-18-10-68	2,626.08
19			09-44-30-30-74	782.60
20			09-44-30-30-75	24.36
21			09-44-36-81-59	2,626.08
22			09-01-02-97-15	1,522.68
			ድምር	**28,724.47**

አባሪ 2፡ በ2013 በጀት ዓመት በተሰጠው የኦዲት አስተያየት መሰረት እርምጃ ያልተወሰደባቸው ግኝቶች፤

ተ.ቁ	የ2013 በጀት ዓመት የኦዲት ግኝቶች	እርምጃ		የተወሰደው እርምጃ	የኦዲተር አስተያየት
		ተወስዷል	አልተወሰደም		
		✓	X		
1	ብር 200,000.00 የክፍያ ማስረጃ ሳይቀርብለት አላግባብ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤		X	የእርምት እርምጃ አልተወሰደም፡፡	በሪፖርት ይገለጽ፡፡
2	ብር 305,500.00 አላግባብ በድጋሚ በወጪ የተመዘገበ መሆኑ፤		X	›› ››	›› ››
3	ብር 1,188.00 ተገቢ ማስረጃ ሳይቀርብለት የስልጠና ወጪ በሚል አላግባብ የተከፈለ መሆኑ፤		X	›› ››	›› ››

የፌዴራል ዋና ኦዲተር መ/ቤት